

# ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ?”

(ከስሜነህ ጌታነህ)

--------------------------

የዛሬ 46 ዓመት ገደማ ፡፡
ታህሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም. ከታናሽ ወንድሙ መኮንን ሲሳይ ጋር በመሆን ከስድስት ኪሎ በስተጀርባ አፍንጮ በር በሚባለው አካባቢ ፍቅረኛውን ዮዲት ታዬን ለመሸኘት ታክሲ ሊያሳፍሯት ወደ መኪና መንገድ ወጡ። ሰዓቱ በግምት ከምሽቱ አንድ ሰዓት ከሩብ ይሆናል። አንድ ታርጋ የሌላት መኪና ቀረብ በማለት የሞት ጥይቷን ጀግናው ወጣት ላይ አርከፈከፈች።
---
በኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ መሪ ቦታ የነበረው ጥላሁን ግዛው በግፍ ተገደለ። ጥላሁንን በመግደል የፊውዳሉን ሥርዓት የግፍ አገዛዝ ዕድሜ ለማራዘም ያለሙት ግድያው ቢሳካላቸውም ትግሉን ሊገድሉት ግን አልቻሉም። በጥላሁን ስም የትግል መፈክሮች ተጻፉ፤ ሌሎች ቆርጠው ተነሱ፤ “ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ?” ተዘመረ።
--
“አትነሳም ወይ! አትነሳም ወይ!
የግፍ አገዛዝ አይበቃህም ወይ”
ጩኸቶች በርካታ ጥላሁኖችን ወለደ።
“ፋኖ ተሰማራ ፋኖ ተሰማራ
እንደሆችሚኒ እንደ ቼጉቬራ”
--
የበርካታዎችን ልብ አሸፈተ። የጥላሁን ድምጽ ከመቃብር ጮኸ፤ “መሬት ለአራሹ” በጥላሁን አጥንት ተገነባ፤ ብሶትና ቁጭት ያንገበገበው ተማሪና ግፍና መከራ የሰለቸው የኢትዮጵያ ሕዝብ የረዥም ጊዜ ትግሉ ውጤት አምጦ አምጦ የካቲት 66 ን ወለደ።

ጥላሁን ግዛው ከአባቱ ከንቡረዕድ ግዛው አበራና ከእናቱ ከወ/ሮ ደሴ አደዬ ረታ በ 1933 ዓ.ም. በራያና ቆቦ አጠርቫ በመባል እምትታወቀው የገጠር መንደር ይወለዳል። ጥላሁን ዕድሜው ለትምህርት ሲደርስ ዕድገቱን በአድረገባት በገጠሯ አጠርቫና ሰንደይ የቤተክህነት ትምህርቱን እስከ ዳዊት ይከታተላል። የመጀመሪያዎቹን ዓመታት ዕድገቱን ከሴት አያቱ ከወ/ሮ ጥሩ ለገሠ ጋር የነበረው ጥላሁን እናቱ ሌላ ትዳር ይይዙና ወደ ላስታ አውራጃ ጊዳኖ ወረዳ ሲጓዙ አብሮ በመሄድ ዕድገቱን ያደርጋል። ጥላሁን ወደ ዘመናዊ ት/ቤት በመዛወር ወልድያ ጣይቱ ብጡል አንደኛ ደረጃ ት/ቤት ጀመረ።

ቀጠን ብሎ ረዘም ያለው ቀይ ሸበላ ወጣት ጥላሁን በመጀመሪያዎቹ አሥራዎቹ ዕድሜው ላይ ከአባቱ ጋር ወደ አዲስ አበባ በመምጣት እንጦጦ ሚሽን አዳሪ ት/ቤት በመግባት የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ተከታተለ። ጥላሁን በማስከተልም የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን ኮተቤ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በከፍተኛ ውጤት በማጠናቀቅ በ 1959 ዓ.ም. የቀድሞው ቀዳማዊ ኃይለ ሥሊሴ (ቀ.ኃ.ሥ) ዩኒቨርሲቲ የአሁኑ አዱስ አበባ ዩንቨርሲቲ ሊገባ ችሎአል።

የልዕልት ሣራ ግዛው ወንድም ጥላሁን ግዛው ከባላባት ቤተሰብ ቢወለድም ዕድገቱ ከገበሬ ልጆች ጋር ነበር። በገጠር ኑሮው ከአካባቢው ሕዝብ ጋር ለመመሳሰል በአለባበሱም ሆነ በባህሪው ይጥራል። በተማሪነት ዘመኑ ጊዜውን የሚያሳልፈው ከመሰል ተማሪ ጓደኞቹ ጋር እንጂ ከባለስልጣንና ከከበርቴ ጋር አልነበረም።

የጥላሁን አንባቢነት ደግሞ የተለየ ነበር። ከቤተክህነት ት/ቤት የጀመረውን የማንበብ ባህል አዲስ አበባ እንጦጦ ሚሽን አዳሪ ት/ቤት ሲገባ ይበልጥ አጎለበተው። የጥላሁን የመማርና የማንበብ ልምድም እየተገነዘበ ከአደገበት የገበሬ ጎስቋላ ሕይወት ጋር በማጣመር የኢትዮጵያን የፖለቲካ አቅጣጫ ለብዙኃኑ በሚስማማ መልክ ለመቀየር ገና በለጋ ዕድሜው ያውጠነጥን ያዘ።

ጥላሁን በቀ.ኃ.ሥ. ዩንቨርሲቲ የሶሻል ሳይንስ ተማሪ በመሆን ባገኘው ከፍተኛ ነጥብ መሠረት የመጀመሪያው ምርጫው ወደ ሆነው የፖለቲካ ሳይንስ የትምህርት ክፍል በመግባት ይበልጥ የሀገሩንና የዓለምን ፖለቲካ በሚገባ በመረዳት ግንዛቤ እንዲያገኝ አረድቶታል።

በኢትዮጵያ የተማሪዎች ትግል ከ 1956 ዓ.ም. ቀደም ሲል የተፈጠረው የግራ ኃይልች አስኳል ተጠናክሮ «አዞዎች» የተሰኘ ስብስብን በመፍጠር 1957 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ተማሪዎች የትግል መርህ «መሬት ላራሹ» መሆኑ ይፋ ተደርጎ መጋቢት 4 ቀን 1957 ዓ.ም.
«መሬት ላራሹን የምትሹ፤
ተዋጉለት አትሸሹ»
እያለ ተማሪዎች በአደባባይ ሰልፍ በወጡ ወቅት የ 11 ኛ ክፍል ተማሪው ጥላሁን በሰልፉ ተሳትፏል።

በኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ጉልህ ስፍራ የያዘው ይህ ቀን ተማሪዎች በኢትዮጵያ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ግንኙነት ትልቅ ሚና በሚጫወተው በመሬት ይዞታ ላይ ማተኮራቸው አዲስ የፖለቲካ ሥርዓትን ለማምጣት እንደሚታገል ያመላከተ ነበር። ለዚህም በኢትዮጵያ ላለው አጠቃላይ ችግር ተጠያቂው የጉልተኛው ሥርዓት መሆኑን አመልካች ነበር።

በወቅቱ ሶሻሊዝም የኢትዮጵያን ችግር የሚፈታ ሥርዓት መሆኑም የበርካታዎችን ድጋፍ አገኘ። ተያይዞም የመጻፍና የመደራጀት መብት ጥያቄዎች ይነሱ ጀመር። የዚህም ትግል ውጤት ዝነኛውን የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ማህበር «ኡዙዋ» USUAA (University Students Union of Addis Ababa) በማስገኘት በኢትዮጵያ ተማሪዎች የፕሬስ ነጻነት ታሪክ ውስጥ ቀዲሚውን ሥፍራ የያዘውን «ታገል» በመባል የሚታወቀውን ልሣን አስገኘ።

ጥላሁን ግዛው የ«አዞዎቹ» ዓላማ አራማጅና በኋላም ለመሪነት ለመታጨት የበቃ ወጣት ነበር። በ 1961 ዓ.ም. በተደረገው የ«ኡዙዋ» ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በመኮንን ቢሻው ቢሸነፍም በቀጣዩ ዓመት ኅዳር 1962 ዓ.ም. በተደረገው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በከፍተኛ ድምጽ ብልጫ ሊያሸንፍ በቅቷል።

ጥላሁን በፕሬዚዳንትነቱ ቀዳሚው ሥራው የተማሪውን የመናገር፣ የመጻፍና የመደራጀት ነጻነት ይበልጥ ማጠናከር ሆነ። ለሁለት ወር ብቻ በፕሬዘዲንትነት ሕይወቱ የኖረው ጥላሁን የተለያዩ ሀሳቦች እንዲንሸራሸሩ በማበረታታቱ የሚታወቅ ታጋይ ነበር። ያ ትውልድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወት መሻሻል ያለምንም ስስት ሕይወቱን አሳልፎ የሰጠ በመሆኑ ትግል የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ሁሉ ለመክፈል ዝግጁ ነበር። ጥላሁን ግዛው ከባላባት ቤተሰቦች የተወለደ ቢሆንም መደቡን ለድሀው ገበሬ፣ ሕይወቱን ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ ክብሩን ለሰንደቅ ዓላማው የሰጠ የዚያ ትውልድ ብርቅዬ ወጣት ነበር።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ትግል መሠረታዊ አቅጣጫ እንዲይዝና የመደራጀት አስፈሊጊነትን የጠቆመ አርቆ አስተዋይ ነበር። ንጉሡ በሽንገላ፣ በምክር፣ በቤተሰባዊ ግንኙነት፣ በቁጥጥራቸው፡ በመዳፋቸው ሊያስገቡት ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉም «እምቢኝ ለሕዝቤ» በማለት ስለ መብትና ነፃነት የተሟገተና በርካታዎችን በአምሳሉ የቀረጸ የዚያ ትውልድ ፍሬ ነበር። ጥላሁን በተማሪው እንቅስቃሴ ውስጥ የጎላ ስፍራ እየያዘ መምጣት ንጉሡና ባላባቱ ጥርስ ውስጥ ገባ። ጥላሁንን በማስወገድ ለሌላው ተማሪ መቀጣጫ በማድረግ ትግሉን ለማለዘብ የንጉሡ ነጭ ለባሾችና የፀጥታ ሠራተኞች በሄደበት ቦታ ሁሉ በመከታተል ያጠኑት፡ ያስፈራሩት ጀመር።

ታላቁ ታጋይ ታህሳስ 19 ቀን 1962 ዓ.ም. አለፈ፤ ጥላሁን ግዛው አረፈ። ከደግነቱ፣ ከታላቅ ተሰጥዎው፣ ከነጥልቅ እውቀቱ፣ ከነብሩኅ ልቡ፣ ከነውብ ተፈጥሮው፣ ከነጀግና ዓላማው፣ ከነሀገር ፍቅሩ…ተከተተ። ለመብት-ለነፃነት-ለእኩልነት-ልእውነት… እንደሰበከ፣ እንደ,ታተተ፣ እንደዋተተ…ተገደለ። ተማሪዎቹ የጥላሁንን አስከሬን ወደ ስድስት ኪሎ የዩንቨርስቲ ቅጥር ግቢ

በመውሰድ ከመላው የአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ከመጡ ተማሪዎች ጋር የሃዘኑ ተካፋይ ሆነዋል።

የጥላሁን ታሪክና የትግል ዓላማ በግጥምና በስድ ንባብ እየተሰማ የሃዘን መግለጫው ዝግጅት እየተካሄደ በቀጣይነት በተማሪዎች ሰልፍ ታጅቦ በክብርና በጀግንነት በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የቀብሩ ሥነ ስርዓት ይፈጸም ዘንድ የዩንቨርስቲው ተማሪዎች ያደረጉት ጥረትና ተጋድሎ በንጉሡ ጸጥታ ኃይሎች አስገዳጅነትና ጭካኔ የተሞላበት እርምጃ ተጨማሪ ተማሪዎችን ሕይወት ቀጥፎ አስከሬኑን ከተማሪዎቹ በመውሰድ አርቆ ለመቅበር የተደረገው ትርኢት ሊታወስ የሚገባው የአገዛዙን ጨካኝነት አመልካች ነበር።

የጥላሁን ግዛው አስከሬን ከተማሪዎቹ በኃይል እርምጃ ከተወሰደ በኋላ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ታህሳስ 22 ቀን 1962 ዓ.ም. በአካባቢው ተማሪዎች ሰልፍ አጃቢነትና መላው ዘመድ አዝማድ በተገኙበት በትግራይ ክፍለ ሀገር በማይጨው ሕዝባ ማርያም ተፈጸመ። ጥላሁን ግዛው በትውልድ ቦታው አንድ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና አንድ መለስተኛ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት በስሙ ተሰይመውለታል።

https://www.youtube.com/watch?v=DpSJ5Xmy0ZE